# ዶ/ር አቢይ በ60ኛ ቀናቸው አዲስ ምእራፍ አበሰሩ

(በወንድወሰን ተክሉ-የኢትዮሚዲያ አምደኛ)

**መንደርደሪያ ነጥቦች-

ሰላም ጤና ይስጥልኝ ውድ እድምተኞቼ እንደምን ሰንብታችኋልሳ?

ለእኔ ይህ የጀመርነው አዲሱ ሳምንትም ሆነ ያለፉት ሳምንታት በታላላቅና ድንቅ ኩነቶች በሀገራችን ፖለቲካ ገበታ ላይ ሲፈጸሙ በደስታ ተሞልቼ እያጣጣምኩ ያለሁበት ሁኔታ በመሆኑ ለእናንተም ተመሳሳይ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፡፡

አዎን-በአሸባሪነትና በመፈንቅለ መንግስት ሙከራ መንግስትን በጠመኛ አፈሙዝ በመገልበጥ ሙከራ ክስ የሞት ፍርድ የተፈረደበት አንዲ- አንዳርጋቸው ጽጌ- ህወሃት መራሹ ስርዓት ከፍተኛ ገንዘብ ለየመኖቹ ከፍሎ ካሳፈነና አንድ ልዩ አንቶኖቮ አይሮፕላን ልኮ ወደ ኢትዮጵ በማምጣት የሞት ፍርዱን ሊፈጽምበት እየጠበቀው ያለውን የጽናት ተምሳሌቱ አንዲ በዶ/ር አቢይ ግልጽና ይፋ ውሳኔ በምህረት ከመፈታቱም በላይ በማግስቱ በታላቁ ቤተመንግስት ተጠርቶ ከጠ/ምኒስትሩ ጋር ከአንድ ሰዓት ተኩል በላይ መወያየት መቻሉን ያየሁበትን ሳምንት በሀገራችን ጉዳይ ላይ ይበልጥ ብሩህ ተስፋን ያየሁበት በመሆኑ ወድጄዋለሁ ብል እናንተን የተከበራችሁ አንባቢዎችን አስከፋ ይሆን?  ብዬ እራሴን ከጠየቅኩ በኋላ የጋራችን በሆነችው ሀገራችን ጉዳይ ደስታዋ ደስታችን ሀዘናም ሀዘናችን ነውና እንደማትከፉ አምኜ ልገልጽላችሁ ወደድኩ፡፡

በዶ/ር አቢይ አመራር በሀገሬ ጉዳይ ያየሁት ብሩህ ተስፋ በሞት ፍረደኛውና ጀግናው አንዳርጋቸው መፈታት ብቻም አይደለም፡፡

የአስቸኳይ ግዜ አዋጁን ጠ/ምኒስትሩ ማንሳት፣የፕ/ር ብርሃኑ ነጋ፣አቶ ጁሃር መሀመድ፣የኢሳትና ኦ ኤም ኤን ላይ በሌሉበት ተከፍቶባቸው የነበረው የሽብር ክስ መቋረጥ፣የመከላከያ ሰራዊት መታደስን አስፈላጊነት መጀመር፣አጠቃላይ የምህረት አዋጅ ረቂቅ መዘጋጀት እና ብሎም በቀደምት ሳምንታት የጠ/ምኒስትሩ ከሶስት ሀገራት ውስጥ ከአራት ሺህ የሚበልጡ ኢትዮጵያዊያን እስረኞችን ከባእድ እስር ቤት ማስፈታት መቻል በዶ/ር አመራር ስር በሀገሬ እንደሚፈጸም ሆኖ ያየሁት የዲሞክራሲያዊ ስርዓት እውን መሆን ታላቅ ተስፋና ደስታን የፈጠረልኝ ክስተት ስለመሆኑ ዛሬ በዚህ ደረጃ ላይ መደበቅ እማይስፈልገኝ ሆናል፡፡

ለመሆኑ ዛሬ ያለንበት አዲሱ ምእራፍ ምን ይመስላል? በዶ/ር አቢይ አመራር ሊታይ የተቻለው ተስፋስ ምን ይመስላል? በዚህ ታሪካዊ ሂደት የእኛስ ድርሻና ምና የትና መቼ ነው እሚገለጸው የሚሉትን ጥያቄ መልስ ያካተትኩበትን የዛሬን መጣጥፌን እነሆኝ ብያለሁ፡፡

**በዶ/ር አቢይ አመራር ሀገራችን ያለችበት አዲስ የሽግግር ምእራፍ

ዶ/ር አቢይ አህመድ ወደ ስልጣን ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እጅግ የተለየ የሆነውን መንግስታዊ አሰራራቸውን እያስተዋወቁን ያሉ መሪ ቢሆኑም የሰሞኑ ግን በእጅጉ የተለየና አመራራቸውንም በአዲስ ታሪካዊ ምእራፍ ጅማሮ ላይ መሆኑን ያየንበትን ውሳኔዎችን ሲያስተላልፉ ለማየት ችለናል፡፡

ይህ ልዩና ታሪካዊ ምእራፍም እኛ ኢትዮጵያዊያን ለዘመናት ስናልመውና ስንታገልለት ወደ ነበረው ሀገራዊ የተረጋጋ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የሚያደርሰን አስደሳችና ተፈላጊ ምእራፍ የመሆኑን ያህልም ይህንን ድል እንዳንጎናጸፍም ቆርጦ በመነሳት እየታገላን ያለው የጸረ ለውጥ ኋይሉ ህወሃትም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ በሞኖፖል ይዞት የነበረውን የበላይነቱን ለማስመለስ እየተዘጋጀ ያለበትን ሁኔታ ስናይ ይህ ቡድን ፋሺታዊ ጥቅሞቹን ለማስጠበቅ እማይፈነቅለው ድንጋይ፣እማይጎነጉነው ሴራና እማይከፍተው የጦርነትና የግጭት አይነቶች እንደሌሉ ከመቼውም ጊዜ በላይ በአንክሮና በንቃት መከታተል ያለብን ጊዜ ቢኖር መቼም ሳይሆን አሁን ብቻ እንደሆነ እንረዳለን ብዬ አምናለሁ፡፡

የዶ/ር አቢይ አመራር ዛሬ አዲስ የታሪክ ምእራፍ ጅማሮን እያበሰረን ያለበት ሁኔታ ላይ ደርሰናል፡፡

ይህ አዲስ ምእራፍ ስኬታማ ይሆን ዘንድ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ድጋፋዊ ሚናን የሚፈልግበት ወቅትና ደረጃ ላይ ያለ ሲሆን የስኬቱ ተጠቃሚም በግንባር ቀደምትነት ሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ከመሆኑ አኳያ እስከዛሬ ካደረግናቸው እልህ አስጨራሽ ትግሎችና መስዋእትነቶች ፍሬያቸውን እንሰበስብ ዘንድ ኋይላችንን እና ድጋፋችንን ሚዛን በዶ/ር አቢይ ዙሪያ የምናሰልፍበት ወቅት ቢኖር ዛሬ እንደሆነ በግልጽና በድፍረት ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

ዛሬ (ማክሰኞ) ፓርላማው ጨቋኙን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ያሽቀነጥራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡  ይህ በህገ ወጥ መንገድ በህዝባችን ላይ ተጭኖ የመከላከያው አግዓዚ በህዝባችን ላይ እንዳሻው እንዲሆን የፈቀደው ጸረ ህዝብ አዋጅ በህወሃት በኩል እንዳይነሳ ብቻ ሳይሆን እንዲራዘምም ጭምር እጅግ በርካታ ሴራና ተግባራቶች ሲፈጸሙ ቢታይም በህዝባችን ጽናትና በዶ/ር አቢይም ያላሰለስ ጥረት የተፈለገው በህዝብና በህዝብ መካከል ጦርነት ሳይነሳ ዛሬ እንዲያውም ያለጊዜ ገደቡ ለመነሳት በቅቷል፡፡

አዋጁን የሚያነሳው ፓርላማ ብሎም በሚቀርብለት ረቂቅ የምህረት አዋጅ ላይም ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጥበታል ተብሎ የሚገመት ሲሆን ረቂቁ የምህረት አዋጅ በጠ/ምኒስትሩ አቅራቢነት በምኒስትሮች ምክር ቤት ተረቅቆ ለመጽደቅ እሚጠባበቅ ሲሆን ይዘቱም በአጠቃላይ መንግስት የፖለቲካውን ምህዳር ለማስፋት የገባውን ቃል እንዲተገብር ያስችለዋል ተብሎ ይታመናል፡፡

ይህ የአዲስ ምእራፍ ብስራት ሲሆን የመከላከያ ሰራዊቱን መልሶ ብሄራዊ መከላከያ ለማድረግ የሚካሄደው ወሳኝ የተሃድሶና የመልሶ ማደራጀት ስራም «ሀ» ተብሎ የሚጀመረበትና እሚተገበርበት ወቅትም ይህ አሁን የጀመርነው ምእራፍ ላይ በመሆኑ ሂደቱን ከባለፉት ሁለት ወራት ቆይታ እጅግ የተለየ፣ ብሎም አጓጊና እንዲሁም አስጊም አድርጎታል፡፡

መከላካያውን ከአንድ ፓርቲ ታማኝነትና ቁጥጥር አላቆ ለሀገርና ለህዝብ ታማኝና ተጠሪ አድርጎ የማዋቀሩ ዓላማ የሚያጓጓው ክፍል ሲሆን የሚያሰጋው ክፍል ደግሞ የነውጠኞቹ ህወሃታዊያን ሴራና ሸር ይህንን ዓላማ እንዳይተገበር ለማድረግ ያላቸው ፍላጎትና ዝግጁነት ነው፡፡

ይህ የእለተ ማክሰኞ የፓርላማው ወሳኝ ቀጠሮ እንደተጠበቀ ሆኖ ሳለ በአንጻሩም ጎን ለጎን የኢህአዴግ ስራ አስፈጻሚ አመራር ኮሚቴ አባላትም ዶ/ር አቢይ ወደ ስልጣን ከመጡ ጊዜ ጀምሮ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደሚሰበሰብ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይህ በፌዴራል ደረጃ እየተከናወነ ባለበት ወቅትና ሁኔታ በህወሃት በኩል ደግሞ መቀሌ ላይ ተሰብስበው ለየት ያለ አቋም በመያዝ እራሳቸውን ምስጢራዊና ለተለ አላማና ግብ ያዘጋጁበትንም ሁኔታ በግልጽ እያየን ያለንበት ወሳኝ ወቅት ላይ እንዳለን መረዳት ይቻላል፡፡

የመቀሌው ስብስብ አብዮታዊ ዲሞክራሲ እየተቀለበሰ ነው በሚል አቋም እራሱን በጸረ ለውጥ ጎዳና ላይ ያሰለፈ ኋይል ሆኖ የተገኘ ሲሆን ይህ ኋይል በበኩሉ ኦህዴድን እና ብአዴንን በጸረ አብዮታዊ ዲሞክራሲ እና በኢህአዴግን የተለምዶ አካሄድ አፍራሽነት በመፈረጅና ብሎም በመወንጀል አይዲኦሎጂውን ከውድቀት መታደግ አለብን ብሎ የተነሳ ኋይል መሆኑን በሚገባ እየነገረን ነው፡፡

«የህወሃት ስርዓት ተጠቃሚ የሆኑ ኋይሎችንና ህዝባችንን ይዘን ይህን ጸረ አብዮታዊ ዲሞክራሲን እርምጃና ሂደቱን መዋጋት አለብን » በማለት አቶ ስዩም መስፍን በጠ/ምኒስትር ዶ/ር አቢይ እና በሚመራው መንግስት የቀረበውን የብሄራዊ ተሃድሶ National Reform በተለይም መካላከያ ሰራዊቱን የተመለከተውን የለውጥ እርምጃ ማክሸፍ እንደፈለጉ ለአባላቶቻቸው በይፋ እየገለጹና ብሎም የተቻላቸውን ድጋፍ ለማሰባሰብ ሲጥሩ ይስተዋላል፡፡

የኤታማዦር ሹሙ ጄ/ል ሳሞራ ዩኑስ ለወይን መጽሄት በሰጡት ቃለ ምልልስ «መከላከያው አዳክሞ ለማፍረስ የሚፈልግ ኋይል አለ፡፡ነገር ግን በሀሳብ ብቻ የሚሆን ስላልሆነ የሚፈጸም አይሆንም» ማለት በቀጥታ ያነጣጠረው በጠ/ምኒስትሩ የመከላከያ ሰራዊቱን ከአንድ ፓርቲ ቁጥጥርና ለአንድ ፓርቲ ታማኝ ታዥነትን አላቅቆ የሀገርና የህዝብ ተጠሪና ታማኝ ለማድረግ የቀረበውን ፕሮግራም «በመቃብሬ/Over my dead body » ካልሆነ በስተቀር እማይታሰብ ነው እሚሉ መስለዋል፡፡

የአንድ ሀገር መከላከያ ሰራዊት ታማኝነት፣ታዛዥነት እና አገልጋይነት ለሀገር፣ለህዝብና ህዝብ ለሚመርጠው መንግስትና ለዚያች ሀገር መተዳደሪያ ህግ ካልሆነና የሰራዊት ታዛዥነትና አገልጋይነት ለአንድ ውስን ፖለቲካዊ ድርጅትና ቡድን ብቻ ከሆነ በዚያች ሀገር ፍትሃዊነትን፣ የህግ የበላይነትን እና የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ማበለጸጊያ ተቋማትን ተበራክተውና ተስፋፍተው ማየት የህልም ያህል እማይጨበጥ ነው፡፡

ሀገራችን ከህዳሩ 2015 የጊንጪ ክተማ ህዝባዊ ዓመጽ ተነስቶ ላለፉት ሁለትና ተኩል ዓመታት ውስጥ በተካሄዱት ከፍተኛ መስዋእትነትን አስከፋይ ህዝባዊ ትግሎች በኦሮሚያና በአማራ ክልል ብቻ ከ8ሺህ በላይ መብታቸውን ጠያቂ ንጽኋን እንደተሰው ይታመናል፡፡

የሰፊው ህዝብም ጥያቄዎች ከፖለቲካ እስረኛ ይፈታ እስከ ፍትሃዊ የህብት ክፍፍል ቢኖርበትም ዋነኛው ጥያቄ ግን ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ህወሃት መራሹ ስር ዓት/ስርነቀል ለውጥ እንፈልጋለን የሚል በመሆኑ ከአራቱ የኢህአዴግ መንግስታዊ ድርጅቶች ውስጥ በኦህዴድና በብአዴን ውስጥ ህዝባዊውን ጥያቄ ፍትሃዊነትን የተቀበለና ለመፈጸምም ቁርጠኛ አቋም ያለው መንግስታዊ የለውጥ ኋይል ሊፈጥር ቻለ፡፡

ይህ በአቶ ለማ መገርሳ፣አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና ዶ/ር አቢይ እሚመራው መንግስታዊው የለውጥ ኋይልም ይህን የህዝብ ጥያቄ ተቀብሎ በማስተጋባትና ለመፈጸምም ቃል በመግባት ዶ/ር አቢይን ለጠ/ምኒስትርነት ካበቃ እነሆኝ ስድሳ ቀናቶችን አስቆጥሯል፡፡

ሀገሪቷ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስር ባለችበት ወቅት መንበር ስልጣኑን የያዙት ዶ/ር አቢይ አህመድ ወሳኙን የስልጣናቸውን ክፍል በወታደራዊው እዝ የተያዘባቸው በመሆኑ ብዙዎች ትርጉም ያለው ስራ ይፈጽማሉ ብለው ባይጠብቁም እሳቸው ግን የሀገሪቷን መጻኢ እድል ላይ በአዎንታዊ ጎን ታላቅ አሻራውን ያኖረ ስራን በመስራት ለዛሬው አዲስ ምእራፍ ስፍራ ላይ ለመድረስ በቅተዋል፡፡

ሆኖም በከፍተኛ አደጋ ላይ ወድቃ በነበረችው ሀገራችን አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋትን ካሰፈኑ በኋላ ወደ መሰረታዊው የሀገሪቷን የፖለቲካ ችግሮች ወደመፍታቱ ለማምራት እቅድና ፕሮግራም

ይዘው እየተንቀሳቀሱ ላሉትና ተስፋ ፈንጣቂ ለሆኑት ዶ/ር አቢይ ዓላማ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ያላቸውን ድጋፍ (88% ኢትዮጵያዊያን በዶ/ር አቢይ አመራር ለውጥ ይመጣል ብለው እንደሚያምኑ የህዝብ አስተያየት ሰብሳቢ ድርጅት አስታውቋል) ቢገልጹም ቁጥሩ አነስተኛ ሆኖ ግን ድጋፉንም ሆነ ተቃውሞውን ለመተግበር ከፍተኛ ኋይል እንዳለው እሚነገርለት ኋይል የጠ/ምኒስትሩን የለውጥ ጥረት ክፉኛ እየተቃወመ እንዳለ እያየንም ነው፡፡

የአራት እራሳቸውን የቻሉ ድርጅቶች ጥምር ውጤት በሆነው በገዢው ኢህአዴግ ውስጥ ዛሬ ሶስት አይነት የተለያዩ ኋይሎች እንደተፈጠሩና መንግስታዊው ድርጅትም በሶስት ኋይሎች ተከፋፍሎ እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

እነዚህም ሶስት ኋይሎች-

1ኛ- የለውጥ ኋይል- በአቶ ለማ መገርሳ የሚመራው ኦህዴድና በአቶ ገዱ የሚመራው ብአዴን ውስጥ የተወሰነው ክፍል የለውጥ ኋይል ሆኖ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን እሚመራውም በፌዴራል ደረጃ በጠ/ም ዶ/ር አቢይና በሁለቱ የክልል ፕሬዚዳንቶች ነው፡፡

2ኛ- የጥገናዊ ለውጥ ኋይሎች-ሙሉ በሙሉ የደህዴህ አባላትን እና ከከፊል ብአዴን እነ በረከት አይነቱን የያዘው ክፍል የጥገናዊ ለውጥ ተንቀሳቃሽ የሆነ ሲሆን ይህ ክፍል በሚካሄደው ማንኛውም ጥገናዊ ለውጥ ስልጣኑና ጥቅማጥቅሞቹን አስጠብቆ መንቀሳቀስ የሚፈልገው ክፍል ሲሆን

3ኛ- ሙሉ በሙሉ የጸረ ለውጥ ኋይል ሆኖ በእሱ ቁጥጥርና መሪነት የጥገናዊው ለውጥ ቢካሄድ እንደሚፈልግ እሚታወቀው የህወሃት ኋይል ናቸው፡፡

ጠ/ምኒስትርነቱን ስልጣን ከያዙ 60ኛ ቀናቸውን የያዙት ዶ/ር አቢይ አህመድ በህወሃት ዘንድ እጅግ ከፍተኛ ውግዘትን እና ተቃውሞን የከፈተባቸውን ሀገሪቷን ወደ ሙሉ የለውጥ ጎዳና የሚያመራትን እርምጃና ውሳኔ በይፋ መውሰድ ሲጀምሩ በትግራይ መቀሌ የከተሙት የህወሃት ኤሊቶች ተሰባስበው ለየት ያለ ውሳኔ ያሳለፉ ሆነው የመገኘታቸው እውነታ የጠ/ምኒስትሩ ለሁለንተናዊ ለውጥ ተነሳሽነት የለውጥ ፈላጊውን እና የሰፊውን ኢትዮጵያ ህዝብ ሁለንተናዊ ድጋፍ የሚሹበት ወቅት እንደሆነ እንረዳለን፡፡

ህወሃት በትግራይ ተሰብስቦ ለአባላቱ እየገለጸ ባለው ገለጻ መሰረት የዶ/ር አቢይን የለውጥ ፕሮግራም ጸረ አብዮታዊ ዲሞክራሲ በሚል ፍረጃ ለማጨናገፍ ያወጣው እቅድ ከሞላ ጎዳል የሚከተለውን ይመስላል፡፡

1ኛ-በኦህዴድና ከፊል ብአዴን የተነሳውን የለውጥ እሳት ለማዳፈን-
«ሀ» ብአዴንን በድርጅቱ ውስጥ ባሉት ታማኝ የህወሃት አገልጋዮች ተጠቅሞ ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር

«ለ» ብአዴንን ለመቆጣጠር የወልቃይትን እና የራያን የማንነት ጥያቄን ተተርሶ ወታደራዊና ካድሬያዊ ዘመቻ መፈጸም

2ኛ-በኦሮሞና አማራ መካከል የጎሳ ግጭት መፍጠር (በማንኛውም ታክቲክና ስልት ተጥቅሞ)

3ኛ-መካላከያውን ከጠ/ምኒስትሩ የተሀድሶ ፕሮግራም መከላከልና ታማኝነቱን ለህወሃት ያደረገን ሰራዊት መያዝ

4ኛ-በማእከላዊው መንግስት ስር እማትገዛን ትግራይን ለመግዛት ከኤርትራ ጋር ፈጣን የእርቅ ሁኔታን መፈጸም (ይህ የአጭር ጊዜ እቅድ ሳይሆን የረዥም ጊዜ ነው)

5ኛ-በዶ/ር አቢይ እና በአመራሩ ላይ የሳይኮሎጂ ጦርነት መክፈት የሚሉት ይገኙበታል፡፡

የህወሃት ጸረ ዶ/ር አቢይ እርምጃዎችና እንቅስቃሴዎች እስከ አሁን (በሁለት ወር ውስጥ)በይፋ ያወጣና በሳቦታጅ መልክ ሲፈጸም የነበረ ሆኖ ሳለ አሁን ግን የዶ/ር በህገ መንግስቱ አንቀጽ 72 ተራ ቁ ከ1-14 ላይ የሰፈረውን የጠ/ምኒስትር ስልጣን ሙሉ በሙሉ ተጠቅመው በህገሪቱ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት መነሳት በህወሃት በኩል በድብቅ ሲካሄድ የነበረውን ተቃውሞ በይፋ እንዲያደርግ እንዳስገደደው ይገመታል፡፡

የጠ/ምኒስትሩን ስልጣን በመቀራመት የዶ/ር አቢይን የመስራት አቅሙ በእጅጉ ሲፈታተን የነበረው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ መነሳት ለጠ/ምኒስትሩ ብቻ ሳይሆን ለሀገሪቷም አዲስ ምእራፍ ከፍታልና የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ንቁ ተሳትፎና ክትትልን ሀገሩ የምትፈልግበት ወቅት ቢኖር ዛሬ እንጂ መቼም አይደለም ስል ጽሁፌን ስደመድም በቸር ያቆየን እያልኩ ከመሰናበቴ በፊት በ24-01-18 በማስታወሻ ደብተሬ ላይ ያሰፈርኩትን ጸሎት መሳይ እመነታዊ አቋሜን ላካፍላችሁ

«የኢትዮጵያ አምላክ ኢትዮፕጵያዊያንን በእኩል ዓይን እያየ በፍትህ፣በእኩልነት፣በአንድነት፣በነጻነት እና በብልጽግና የሚመራ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት ብሎም በኢትዮጵያ ታሪክና አንድነት የሚያምን ኢትዮጵያን አፍቃሪ መንግስት/መሪ እንደሚሰጠን አምናለሁ፡፡
ኢትዮጵያ አንድነታን ጠብቃ በሰላም፣በፍቅርና በብልጽግና ለዘላለም ትኑር» በሚል ያሰፈርኩ ሲሆን ይህን እምነታዊ አቋሜን አምላክ አይቶ ዶ/ር አቢይን የሰጠን ስለመሆኑ በጽናት መናገር ጀምሬያለሁ፡፡

-----------------

ጥቆማና አስተያየታችሁን በteklu7@gmail.com ጻፉልኝ እመልሳለሁ

--

Ethiomedia.com
June 4, 2018